የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 21
ADDIS ABABA 17th Feburary 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፯/፪ሺ፮ ዓ.ም

ለሞጆ-ሐዋሳ መንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ............................................ገጽ ፯ሺ፪፻፶፯

CONTENTS

Proclamation No. 827/2014

African Development Fund Financing Agreement for Financing Modjo-Hawassa Highway Project Phase I Ratification Proclamation ......... Page 7257

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፯/፪ሺ፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለሞጆ-ሐዋሳ መንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፹፬ ሚሊዮን ፹ሺ ዩ.ኤ. (ሰማኒያ አራት ሚሊዮን ሰማኒያ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፮ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንን የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሞጆ-ሐዋሳ መንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፯/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 827/2014.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 84,080,000 U.A. (eighty four million eighty thousand Units of Account) for financing the Modjo-Hawassa Highway Project Phase I was signed in Addis Ababa on the 6th day of December, 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 28th day of January, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Financing Agreement for Financing Modjo-Hawassa Highway Project Phase I Ratification Proclamation No. 827/2014".

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ. ዲሴምበር ፮ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 2100150030195 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፹፬ ሚሊዮን ፹ሺ ዩ.ኤ. (ሰማኒያ አራት ሚሊዮን ሰማኒያ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement Number 2100150030195 signed in Addis Ababa on the 6th day of December, 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 84,080,000 U.A. (eighty four million eighty thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of February, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት